ጉዳዩ:- <u>በጄኔቭ ሚሽን የግንቦት 20 በዓል በደማቅ ሁኔታ ስለመከበሩ፤</u>

የኢፌዲሪ የጄኔቫ ቋሚ መልዕክተኛ ጽ/ቤት የግንቦት 20ን በዓል በደማቅ ስነ ስርዓት ሰኔ 5 ቀን 2002 ዓ.ም. አከበረ:: በበዓሉ ላይ የሠራተኛ ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስትር ክቡር አቶ ሀሰን አብደላን ጨምሮ በስዊስ የሚኖሩ ኢትዮጵያውያንና ትውልድ ኢትዮጵያውያን ተገኝተዋል::

በበዓሉ ላይ ንግግር ያደረጉት የሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስትር ክቡር አቶ ሐሰን አብደላ «የዘንድሮው ግንቦት 20ን የምናከብረው 4ኛውን አገራዊ ምርጫ ባካሄድንበት ማግስት በመሆኑ ከመቸውም በላይ ለየት ያደርገዋል::» ብለዋል:: መንግስት ምርጫውን ሰላማዊ፤ ፍትሀዊ፤ ዲሞክራሲያዊና በህዝብ ዘንድ ተዓማኒ ሆኖ እንዲጠናቀቅ ዘርፈ ብዙ ተግባራትን ማከናወኑን የተናገሩት ሚኒስትሩ፤ ህዝቡ ከቀረቡለት አማራጮች መካከል በሰከነና ምክንያታዊ በሆነ መንገድ ድምፁን ይወክለኛል ላለው ፓርቲ መስጠቱን ገልጸዋል::

በተጨማሪም ክቡር አቶ ሐሰን በአገራችን ባለፉት አራት ዓመታት በአማካይ 11.18% በላይ የኢኮኖሚ ዕድገት መመዝገቡን፤ በጤና፤ በትምህርትና በመሠረተ ልማት ዘርፎችም ከፍተኛ ለውጦችን ማስመዝገብ መቻሉን ተናግረዋል:: መንግስት አሁንም ከአገራችን ድህነትን ለማጥፋት ያለውን ቁርጠኝነት ያረጋገጡት ሚኒስትሩ፤ ለዚህም ለሠላም፤ ለልማትና ለዲሞክራሲ ከሚሰሩ ወገኖች ጋር ለመስራት ያለውን ዝግጁነት ገልጸዋል::

ሚኒስትሩ «በአገራችን በተመቻቸው የንግድና የኢንቨስትመንት ሁኔታ ተጠቅማችሁ እራሣችሁንና ወገናችሁን እንድትረዱ ጥሪዬን በኢትዮጵያ መንግስት ስም አቀርባለሁ» ሲሉ ለበዓሉ ተዳሚዎች ጥሪያቸውን አስተላልፈዋል:: በመጨሻም ክቡር አቶ ሐሰን አብደላ የጄኔቫ ሚሽን በዓሉን በደማቅ ሁኔታ በማዘጋጀቱ ምስጋናቸውን አቅርበዋል::

በበዓሉ ላይ በመገኘት ንግግር ያደረጉ አቶ ታደለ ይመር፤ የኢትዮጵያ አሠሪዎች ፌዴሬሽን ፕሬዚዳንትና የኢትዮጵያ የሲቪል ማህበረሰብ ጥምረት ሊቀመንበር፤ ጥምረቱ ምርጫውን መታዘቡን አውስተው፤ በዚህም ምርጫው ዲሞክራሲያዊ፤ ነፃና ፍትሃዊ እንደነበር ላረጋግጥላችሁ እወዳለሁ ብለዋል:: አቶ ታደለም በስዊስ የሚገኙ ኢትዮጵያውያንና ትውልድ ኢትዮጵያውያን በተመቻቸው የአገራቸው ሁኔታ ገብተው ኢንቨስት እንዲያደርጉ ጥሪያቸውን አቀርበዋል::

በዓሉ የተከበረው በጄኔቫ ቋሚ መልዕክተኛ ጽ/ቤት የአምባሳደሩ መኖሪያ ቤት ሲሆን በስነ ስነስርዓቱ ኢትዮጵያውያንና ትውልድ ኢትዮጵያውያን ያገናኘና ስለአገራቸውም ሀሳብ እንዲለዋወጡ ያስቻለና በደማቅ ሁኔታ የተካሄደ ነበር::

በበዓሉ ላይ የሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስትር ዴኤታ ክብርት ወ/ሮ ዘነቡ ታደሠና የኢትዮጵያ የሠራተኞች ማህበራት ኮንፌዴሬሽን ፕሬዚዳንት አቶ ካሣሁን ፎሎ ተገኝተዋል::

ከሠላምታ ጋር

ልዑልሰገድ ታደሠ
ሦስተኛ ፀሐፊ